# ጋዜጣዊ መግለጫ

የአሜሪካን ኤምባሲ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
*2016/43*

ለተጨማሪ ማብራሪያ 011-130-7033 ይደውሉ
http://ethiopia.usembassy.gov ድረ-ገፅን ይጎብኙ

## የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ በተሻለ የጤና አቅርቦት ሰንሰለት ህይወትን ታድጓል

መስከረም 19 ቀን 2009 ዓ.ም.፤ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፡- የአሜሪካ መንግሥት በአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ (ዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ) በኩል ለ10 ዓመታት በ283 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ሲተገብር የነበረውን የSupply Chain Management System (SCMS) ፕሮጀክት በዛሬው ቀን መዘጋቱን አስታውቋል፡፡ በዚህ ፕሮጀክት አማካኝነት የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ የጤና ጥበቃ ሚንስትርን የጤና አቅርቦት ሰንሰለት በማጠናከር የኤች አይ ቪ መድሀኒቶች፣ የላቦራቶሪ መገልገያዎች፣ በሐኪም ትዕዛዝ የሚዘጋጁ ምግቦች (ለተጎዱና ከኤች አይ ቪ ጋር ለሚኖሩ ሰዎች የሚሆኑ ገንቢ ምግቦች)፣ ኢንፌክሽን መከላከያ እና ሌሎች የሕክምና መገልገያዎች አቅርቦት ዙርያ የአቅም ግንባታ ስራ አከናውኗል፡፡

ከ ሕዳር 1999 ዓ.ም. ጀምሮ የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ Supply Chain Management System (SCMS) ፕሮጀክት ከ President's Emergency Plan for AIDS Relief (PEPFAR) ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ 3,200 ኤች አይ ቪ ህክምና፣ ገንቢ ምግቦች እና ኤች አይ ቪ ከእናቶች ወደ ህጻናት እንዳይተላለፍ የመከላከል አገልግሎት ለሚሰጡ የጤና ተቋማት ድጋፍ የሰጠ ሲሆን ከ16,000 በላይ ለሚሆኑ የጤና ባለሙያዎች በተለያዩ የአቅርቦትና የሥርጭት ሥርዓት ዘርፎች ላይ ሥልጠና ሰጥቷል፡፡ የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ በ224 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር መድሀኒቶችንና መገልገያዎች በመግዛት 400,000 ለሚሆኑ ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ሰዎች የሚሰጠውን የተለያየ አገልግሎት በማሳደግ ዙሪያ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ የተቀናጀ የመድሀኒት አቅርቦት ሥርዓት ንድፍ በማዘጋጀት እና በመተግበር ሂደት ድጋፍ በመስጠት ከጤና ተቋማት የሚላኩ የመድሀኒት አቅርቦት መረጃዎች ወቅቱን ጠብቀው እንዲደርሱ አስተዋጽዖ አድርጓል፡፡ የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ የመድሀኒት ፈንድ እና አቅርቦት ኤጀንሲን የክምችትና ስርጭት አቅም በ51,600 ሜትር ኪዩብ (30,000 የፓሌት ስፔስ) ሲያሳድግ 74 ከባድ የጭነት፣ አምስት የመስክ ተሽከርካሪዎች፣ አምስት የሞተር ብስክሌቶች፣ 22 ዕቃ ማውጫና ማውረጃ ፎርክሊፍቶች፣ የተለያዩ የመጋዘን ውስጥ ዕቃ ማንቀሳቀሻ መሣሪያዎች እና 15 ጄኔሬተሮችን በመስጠት የትራንስፖርት አገልግሎቱ እንዲሳለጥ አድርጓል፡፡

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ ሚሽን ዳይሬክተር ሌስሊ ሪድ Partnership for Supply Chain Management እና Management Sciences for Health የተባሉትን አጋር ደርጅቶች የኢትዮጵያን የአቅርቦት ሰንሰለት ለማሻሻል ያደረጉትን ያላሰለሰ ጥረት በማድነቅ በ Supply Chain Management System (SCMS) ፕሮጀክት የተገነባውን ጥረት Global Health Supply Chain - Procurement and Supply Management በተባለ ፕሮጀክት የሚቀጥል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከመድሀኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ፣ ከኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት፣ ከኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት፣ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ፣ ከድሬዳዋ አስተዳደር ጤና ቢሮ፣ እና ከዘጠኙ የክልል መንግሥታት የጤና ቢሮዎች ጋር የአቅርቦት ሰንሰለት ፕሮጀክትን ለመገንባት በቅርበት ሲሰራ ቆይቷል፡፡